የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፱
አዲስ አበባ ህዳር ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 9
ADDIS ABABA, 6th December, 2023

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፬/፪ሺ፲፮

ለውሃ እና ኢነርጂ ዘርፍ ለተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ………………………………………….. ገጽ ፲፭ሺ፪፻፹፮

## Content

Proclamation No. 1304/2023

Italian Republic Loan Agreement for financing Basin Scale Resilience Initiative for Ethiopia Project Ratification Proclamation ……………………...........................Page 15286

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፬/፪ሺ፲፮

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለውሃ እና ኢነርጂ ዘርፍ ለተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ሃያ አራት ሚሊዮን ዩሮ (፳፬ ሚሊዮን ዩሮ) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ፫ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ጥቅምት ፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሄደው ፩ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO. 1304/2023

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF ITALIAN REPUBLIC

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between The Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and The Government of the Italian Republic stipulating that the Government of the Italian Republic shall provide to The Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to Twenty Four Million Euro (Euro 24,000,000.00) for financing Basin Scale Resilience Initiative for Ethiopia Project, was signed in Addis Ababa on 9th Day of March, 2023;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of The Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its 3rd year working period, 1st ordinary session held on 12th Day of October, 2023;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “ለውሃ እና ኢነርጂ ዘርፍ ለተቀናጀ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፬/፪ሺ፲፮” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር F.ROT/AID 22/002/00 በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

**፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ሃያ አራት ሚሊዮን ዩሮ (፳፬ ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW,THERFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the “Italian Republic Loan Agreement for financing Basin Scale Resilience Initiative for Ethiopia Project Ratification Proclamation No. 1304/2023”.

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement Number F.ROT/AID 22/002/00 signed in Addis Ababa on 9th Day of March, 2023 between The Government of Federal Democratic Republic of Ethiopia and The Government of the Italian Republic is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan an amount equivalent to Twenty Four Million Euros (Euro 24,000,000.00) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 7th Day of December, 2023**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**